በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ

በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት



አዲስ በተሻሻለው የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 ለግብር ከፋይ የሂሳብ ባለሞያዎች እና ለሴት ግብር ከፋዮች የተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና፤

ግንቦት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

WELL COME !!!

በሰነዱ የተካተቱ ዋና ዋና አርእስት

1) **መግቢያ**

- የሂሳብ መዝገብ መመሪያ ቁጥር 176/2014 መዉጣት አስፈላጊነት፤
- IFRS እና ለታክስ ዓላማ ስለሚዘጋጅ ሂሳብ መግለጫ፡

2) **የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር *176/2014***

- ከቀድሞዉ የሂሳብ መመዝገብ አያያዝ መመሪያ አንጻር ሲታይ፤

3) **የታክስ ሂሳብ መዝገብ እና የሂሳብ መግለጫ ይዘት**

- የታክስ ሂሳብ መዝገብ ይዘት
- የቤት ኪራይ ገቢ፤
- የካፒታል ሀብቶችን ስለማስተላለፍ፤
- የግብር ሰንጠረዦች
- የታክስ ሂሳብ መግለጫ
- የታክስ ሂሳብ መግለጫ ላይ ስለሚደረግ ማስተካከያ፤
- የታክስ ስሌት ስህተትን ስለማረም፤

ክፍል-1-

መግቢያ

1. መግቢያ

1.1 የታክስ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 መውጣት አስፈላጊነት፤

- ግብር ከፋዩ የሚይዘዉ ሂሳብ መዝገብ ሊያሟላ የሚገባዉን ዝርዝር ሁኔታ ነባሩ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 152/2011 ላይ በግልጽ ባለመቀመጡ፡፡
- ሁሉም የታክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የታክስ የሂሳብ አያያዝን በተመለከተ ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ፡፡
- በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 82(7) እና በፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀፅ 58(1) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን መመሪያ ማዉጣት ስለሚችል ነዉ፡፡

1.2. የታክስ ሂሳብ መዝገብ እና ሂሳብ መግለጫ፤

ሀ) የታክስ ሂሳብ መዝገብ ፡-

- ሁሉንም የፋይናንስ ግብአቶች እና በንኡስ ምድቦች ዉስጥ የተከፋፈለ ሁሉንም የገንዘብ ልዉዉጦች የሚያሳይ ሆኖ፤ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራ ሀብት እና እዳ እንዲሁም የእለት ተእለት ገቢዉን ወጭዉን የሚመዘግብት (Journal & Ledger) ነዉ።

ለ) የታክስ ሂሳብ ሂሳብ መግለጫ፡-

- የግብር ከፋዩ የንግድ እንቅስቃሴ ደረጃ ያለበትን የሚያሳይ ሰነድ ሲሆን፤- የሀብት እና እዳ መግለጫ፤ የገቢ እና ወጭ መግለጫ፤ የገንዘብ ፍሰት እንቅስቃሴ መግለጫ፤ የትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ፤ የምርት ሂደት መግለጫ እና የምርት ወጭ መግለጫ የሚያካትት ነዉ።

ሐ) ጊዜያዊ የታክስ ሂሳብ መዝገብ፡-

- ማንኛዉም ግብር ከፋይ የድርጅቱን ግዥ እና ሽያጭ የሚመዘግብበት ሊኖረዉ የሚገባ የሂሳብ መዝገብ ነዉ።

1.3 FRS እና የታክስ ሂሳብ መዝገብ

- እንደሚታወቀዉ አገራችን በአዋጅ ቁጥር 847/2014 እ.ኤ.አ የአለምአቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃ /International Financial Reporting Standards/ ወይም IFRS የተቀበለች አገር ናት።
- ሆኖም ከዚህ አዋጅ በፊት እና እስከ አሁንም (በተለይም የቅ/ጽ/ቤታችን ግብር ከፋዮች) ጭምር ወደ ስርዓቱ በመግባት ላይ ያሉ እንጅ በሙሉነት ያልተከናወነ እና ለዚሁም ባለቤት የሆነዉ የመንግስት ተቋም የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የሚከታተለዉ ጉዳይ ነዉ። ስለሆነም IFRS በሙያዊ እይታ ሲታይ አለማቀፋዊ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርቲንግ ስለሆነ ለጠቅላላ/General Purpose/ የሚዘጋጅ እንጅ ለታክስ ፤ለአባደሪዎች፤ ለባለቤቶች ለባለድርሻ አካላት ተብሎ የተለየ አይደለም ይህንኑ ሪፖርትን የአጠቃቀም ደረጃና ቅደም ተከተል ግን ሊለያይ ይችላል።
- ስለሆነም እንደ መሰረት/Conceptual/ IFRS እንደ ሀገር የምንጠቀም ቢሆንም በተለይም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በህጉ ሂሳብ መዝገብ መያዝ የማይገደዱት እና የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ቀላል የሂሳብ አያያዝ ስርዓት የሚከተሉት በሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ጭምር IFRS (Either Full Version ወይም IFRS for SMEs/ እንደማይጠቀሙም የሚታወቅ ሲሆን፤ ለግብር/ታክስ የሚዘጋጀዉ የሂሳብ መግለጫ ለጠቅላላ አገልግሎት/IFRS for General Purpose/ ያዉና አንድ አለመሆኑን ከመገንዘብ ባለፈ በአገራችን ብቻ ሳይሆን በሌሎች አገሮች ያለዉ እዉነታ ይኸዉ ነዉ።

1.4 IFRS…

What was Denoted in IFRS Foundation.

- "*IFRSs are designed to apply to the general purpose financial statements and other financial reporting of profit-oriented entities. Profit-oriented entities include those engaged in commercial, industrial, financial and similar activities, whether organized in corporate or in other forms. They include organizations such as mutual insurance companies and other mutual co-operative entities that provide dividends or other economic benefits directly and proportionately to their owners, members or participants*".

The following terms are used in this Standard with the meanings specified:

- ***Accounting profit*** is profit or loss for a period before deducting tax expense. ***Taxable profit (tax loss)*** is the profit (loss) for a period, determined in accordance with the **rules *established by the taxation authorities***, upon which income taxes are payable (recoverable). *Tax expense* (*tax income*) is the aggregate amount included in the determination of profit or loss for the period in respect of current tax and deferred tax. Current *tax* is the amount of income taxes payable (recoverable) in respect of the taxable profit (tax loss) for a period. *Deferred tax liabilities* are the amounts of income taxes payable in future periods in respect of taxable temporary differences.

ክፍል-2-

የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014፤
ከቀድሞዉ መመሪያ ቁጥር 152/2011 አንጻር ሲታይ፤

2.1የአዲሱ የታክስ ሂሳብ መዝገብ ከቀድሞዉ አንጻር ?

- የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 ከቀድሞዉ የሚለይበት በመግቢያዉ ላይ በዝርዝር የተገለጸ ነዉ። ስለሆነም ለማሳያነት እንደሚከለተለዉ አቅርበነዋል።

ተ.ቁ	ዝርዝር ሁኔታ	የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014
1	የመመሪያ ስያሜ	የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ
2	ግ/ከፋዩ መያዝ ያለበት ሰነድ (አንቀፅ-7)	ከቀድሞዉ ዘርዝር ብሎ የቀረበ ነዉ
3	ግብር ከፋዩ የሚይዘዉ የታ/ሂ/መዝገብ(አን-8)	ከቀድሞዉ ዘርዝር ብሎ የቀረበ ነዉ
4	የንግድ እቃቆጠራ (አን-9)	ከቀድሞዉ ዘርዝር ብሎ የቀረበ ነዉ
5	እዳ እና ተከፋይ ሂሳብ (አን-11)	ከቀድሞዉ ዘርዝር ብሎ የቀረበ ነዉ
6	የተከፈለ የደመወዝ ወጭ (አን-18)	የቴምብር ቀረጥ መቅረብ ስላለበት
7	ሰነድ በሚመለከተዉ አካል ማስመዝገብ (አን-19)	የ3 ወር ጉዳይ እና ቴምብር ቀረጥ
8	ሂሳብ መዝገብ ዉድቅ ማድረግ(አን-24)	IFRS-ከቀድሞዉ በተጨማሪነት አለ

2.1 የታክስ የሂሳብ መዝገብ...

ተ.ቁ	ዝርዝር ሁኔታ	የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014
9	የዉጭ ምንዛሬ እና የዋጋ ልዩነት (አን-27)	በአስመጭና ላኪ ላይ በዝርዝር የታየ
10	በግብር ዘመናት ስለተገኘ ብድር	በአዲስ መልክ የቀረበ
11	የተወገደ እቃን በወጭነት ስለመመዝገብ (አን-29)	በቀድሞ መመሪያ አንቀጽ 24-31 የነበረ ሲሆን፤ በአሁኑ በመሸጋገሪያ ድንጋጌዉ አዲስ መመሪያ እስኪወጣ እንዲቀጥል የተፈቀደ
12	ስህተትን ስለማረም (አን-29)	በቀድሞ መመሪያ አንቀጽ 37 የነበረ ሲሆን ፤ በአሁኑ በመሸጋገሪያ ድንጋጌዉ አዲስ መመሪያ እስኪወጣ እንዲቀጥል የተፈቀደ
13	ጥቅል የእርጅና ቅናሽ (አን-29)	በቀድሞ መመሪያ አንቀጽ 38 የነበረ ሲሆን፤ በአሁኑ በመሸጋገሪያ ድንጋጌዉ አዲስ መመሪያ እስኪወጣ እንዲቀጥል የተፈቀደ

2.2 የታክስ ሂሳብ መዝገብ...

የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር *176/2014* ከቀድሞዉ መመሪያ ቁጥር *152/2011* ጋር ለማነጻጸሪያነት ከላይ በሰንጠረዡ የተመለከቱት የተወሰኑ አንቀጾችን ያቀረብን ሲሆን፤ ዘርዘር በማድረግ እንደሚከተለዉ ይቀርባሉ።

<u>ሀ) ግብር ከፋዩ ሰነድ መያዝ ያለበት ሰነድ(አን-7-</u>)

- **የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸዉ፤ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እና በዜሮ-ሬት ያላቸዉን አቅርቦቶች እና ሽያጭ ዋጋ ዝርዝር እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ እና ከዓመታዊ ገቢ ማስታወቂያ መካከል ላለ ልዩነት የተሰራ የማስታረቂያ የሂሳብ ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል።**
- **የተርን ኦቨር ታክስ እና የኤክሳይዝ ታክስ ሰነድ (ለሚመለከታቸዉ)፤**
- **የተለያዩ ፕሮጀክቶች የተከናወኑ ከሆነ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት የወጣ ገቢ እና ወጭ፤**
- **የታክስ ሂሳብ መዝገብ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ሌላ አስፈላጊ ሰነድ መቅረብ ይኖርበታል።**

2.2 የታክስ ሂሳብ....

ለ) ግብር ከፋዩ የሚይዘዉ የታ/ሂ/መዝገብ (አን-8)

- በፕሮጀክቶች የሚከናወን የኮንስትራክሽን ስራ ከሆነ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የታክስ ሂሰብ መዝገብ መያዝ አለበት።

ሐ) የንግድ እቃ ቆጠራ/Stock Inventory) (አን-9-)

- የንግድ እቃ ሲመዘገብ ጥቅም ላይ የዋለ መለኪያን ለመቀየር ቢያስፈልግ መለኪያን መቀየር ያስፈለገበትን ምክንያት እና የተደረገዉን ማስተካከያ፤ ማስተካከያዉ በተደረገ በ30 ቀናት ዉስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል።
- የንግድ እቃዎች በቆጠራ ጊዜ የተመዘገቡበት ስም እና በሽያጭ ወቅት የሚመዘገቡበት ስም ተመሳሳይ መሆን አለበት።

2.2 የታክስ ሂሳብ...

<u>መ) እዳ እና ተከፋይ ሂሳቦች መዝገብ (አን-11-)</u>

- ግብር ከፋዩ የተበደረዉን ገንዘብ ለንግድ ስራ ካላዋለዉ ወጭዉ ተቀባይነት ስለማይኖረዉ፤ ለንግድ ስራዉ እንዳዋለዉ የሚያሳይ ሰነድ መኖር አለበት።
- ግብር ከፋዩ ብድሩን የተበደረዉ ከፋይናንስ ተቋም ወይም የፋይናንስ ተቋም ካልሆነም የተበደረዉም ቢሆን፤ዉሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ወቅት የቴምብር ቀረጥ ስለመከፈሉ ሰነድ መቅረብ ይኖርበታል። ሆኖም ያልተከፈለ ከሆነ እና በመረጃነት ሲቀርብ ሁለት እጥፍ ቀረጥ የተከፈለበት መሆን አለበት።
- ብድሩ በፋይናንስ ተቋም ካልሆነ በስተቀር የወለድ ወጭ ለመያዝ ተገቢዉ ግብር በሰንጠረዥ "መ" ስለመከፈሉ የሚያሳይ ማስረጃ ሊኖር ይገባል።

2.2 የታክስ...

<u>ሠ) የተከፈለ የደመወዝ እና ተያያዝ ወጪ (አን-18)</u>

- ✓ በቴምብር ቀረጥ ህግ መሰረት በቅጥር ዉል ስምምነት ላይ ዉል ከመፈረሙ በፊት፤ ወይም በሚፈረምበት ጊዜ ለተከፈለ ቀረጥ የሚያስረዳ ሰነድ መቅረብ አለበት። በዚሁ መሰረት የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለበት ከሆነ ዉሉ ተቀባይነት የሚያገኘዉ ሁለት እጥፍ ቀረጥ ከተከፈለበት ነዉ።

<u>ረ) ሰነድ በሚመለከተዉ አካል ስለማስመዝገብ (አን-19</u>)

ከዚህ በታች የተገለጹት ዉሎች ሲፈጸሙ ከ3 ወር በላይ ከሆኑ በሚመለከተዉ አካል መመዝገብ አለባቸዉ፦

- ❖ ለንግድ የሚዉል የቤት ኪራይ
- ❖ የመጋዘን ኪራይ
- ❖ የጥናት አገልግሎት ግዥ
- ❖ የማሽነሪ ኪራይ እና የተሸከርካሪ ኪራይ

2.2 የታክስ....

- ታክስ ከፋዩ ከላይ የተጠቀሱት አገልግሎቶች ለማግኘት የሚያደርገዉ ስምምነት አገልግሎቱን የሚሰጠዉ ሰዉ እነዚህን አገልግሎቶችን ለመስጠት የንግድ ስራ ፍቃድ ያለዉ እና ሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ የተጣለበት ከሆነ ዉሉ መመዝገብ ሳያስፈልገዉ ለአገልግሎት የሚያቀርበዉ ህጋዊ ደረሰኝ እና ለአገልግሎቱ የተከፈለዉ **ክፍያ በባንክ ተፈጽሞ ከሆነ በቂ ነዉ።**
- አገልግሎቱ ከመንግስት መ/ቤት ጋር ከሆነ ዉሉ መመዝገብ አያስፈልገዉም።
- በሚመለከተዉ አካል ያልተመዘገበ ሰነድ በሚቀርብበት ጊዜ ተቀባይነት ለማግኘት በቴምብር ቀረጥ ህግ መሰረት ሁለት እጥፍ ይከፈልበታል።

2.2 የታክስ ሂሳብ...

ሰ) የሂሳብ መዝገብ ተቀባይነት የሚያጣበት ሁኔታ(አን-24)

- በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች መሰረት የተዘጋጀ የሂሳብ መግለጫ መቅረብ እየተገባዉ ካልቀረበ፤ (**IFRS-**International Financial Reporting Standard)

ሸ) የዉጭ ምንዛሬ እና የዋጋ ልዩነት (አን-27)

- _ግብር ከፋዩ እቃ ወደ ሐገር በሚያስገባበት ጊዜ በLetter of Credit ሲከፈል በነበረዉ የዉጭ ምንዛሬ ልዩነት እና እቃዉ ወደ ሀገር ሲገባ ባለዉ የዉጭ ምንዛሬ መካከል ያለዉ ልዩነት በሂሳብ መመዝገብ ላይ የተመዘገበ መሆን አለበት።
- እቃ ወደ ዉጭ የሚልክ ግብር ከፋይ ለጉምሩክ ባሳወቀዉ የእቃ መሸጫ ዋጋ እና በባንክ በተላከዉ የመሸጫ ዋጋ መካከል ያለዉ የዉጭ ምንዛሩ ልዩነት በሂሳብ ላይ መመዝገብ አለበት።

እቃ ወደ አገር ዉስጥ የሚያስገባ ግብር ከፋይ ለጉምሩክ ያቀረበዉ የግዥ ኢንቮይስ፡-

2.2 የታክስ ሂሳብ...

1) መጠኑ ጉምሩክ ከሰጠዉ ዋጋ ያነሰ ሆኖ ዉድቅ በሚደረግበት ጊዜ ግብር ከፋዩ የእቃዉን የአገርዉስጥ የመሸጫ ዋጋ ሲወስን ጉምሩክ ለእቃዉ የሰጠዉን ዋጋ መነሻ ማድረግ ያለበት ሲሆን ሌሎች ወጭዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ የእቃዉ የመግዣ ዋጋ ተደርጎ መወሰድ ያለበት ጉምሩክ ለእቃዉ የሠጠዉ ዋጋ ስለሆነ በዚህ አግባብ የተከናወነ ስለመሆኑ ማስረጃ መቅረብ አለበት።

2) መጠኑ ጉምሩክ ከሰጠዉ ዋጋ የሚበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ግብር ከፋዩ የእቃዉን የአገርዉስጥ መሸጫ ዋጋ ሲወስን የግዥ ኢንቮይስ ዋጋ መነሻ ማድረግ ያለበት ሲሆን ሌሎች ዎጭዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ የእቃዉ የመግዣ ዋጋ ተደርጎ መወሰድ ያለበት የግዥ ኢንቮይስ ዋጋ ስለሆነ በዚህ አግባብ የተከናወነ ስለመሆኑ ማስረጃ መቅረብ አለበት።

2.2 የታክስ ሂሳብ...

ከላይ ያለዉ የተገለጸ ቢሆንም፥-

በጊዜያዊነት ወይም ከቀረጥ ታክስ ነጻ ለሚገባ እቃ የእቃዉ የመግዣ ዋጋ ተደርጎ መወሰድ ያለበት ጉምሩክ የትመና ስርዓቱን ተከትሎ ለእቃዉ የሰጠዉ ዋጋ ስለሆነ በዚህ አግባብ የተከናወነ ስለመሆኑ ማስረጃ መቅረብ አለበት።

ቀ) በግብር ዘመኑ ስለተገኘ ብድር (አን-28)

- ግብር ከፋዩ በግብር ዘመኑ የተበደረዉ ብድር በባንክ በኩል የተላለፈለት መሆን አለበት።
- ግብር ከፋዩ ብድሩ ለንግድ ስራ እንቅስቃሴ የዋለ ወይም ከንግድ ስራ እንቅስቃሴዉ የተገኘ ስላለመሆኑ የማስረዳት ሃላፊነት የተበዳሪዉ ነዉ።
- የታክስ ባለስልጣኑ ብድሩ ለንግድ ስራ እንቅስቃሴ የዋለ ወይም ከንግድ ስራ እንቅስቃሴ ስለመሆን ወይም አለመሆኑ በሚቀርበዉ ማስረጃ መሰረት ያጣራል

2.2 የታክስ ሂሳብ

በ) የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 152/2011 በክፍል ሶስት የተወገደ እቃን በወጭነት ስመመዝገብ በተመለከተ ከአንቀጽ 24-31 የተደነገጉ ድንጋጌዎች እና አንቀጽ 37 ወይም 38 በሚወጣ ሌላ መመሪያ ዉስጥ ተካተዉ እስኪወጡ ድረስ ተፈጻሚነታቸዉ ይቀጥላል።

ክፍል-3-

የታክስ ሂሳብ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ ይዘት፤

3. የታክስ ሂሳብ መዝገብ እና የሂሳብ መግለጫ ይዘት፤

3.1 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ለግብር/ታክስ ዓላማ፤

- ግብር ከፋዮች የሂሳብ ለመያዝ የግብር ከፋይ ደረጃቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፥- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ-10 ጀምሮ የተመላከቱት ሰንጠረዦች (ከሰንጠረዥ " ሀ" እስከ ሰንጠረዥ " ሠ" እንደየገቢ አይነቶቹ <u>በተናጠል</u> የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይኖርበታል።
- ስለሆነም የኪራይ ገቢ በተጨማሪነት ያለዉ ግብር ከፋይ ከሰንጠረዥ " ለ" በመሆኑ ከሰንጠረዥ " ሐ" ለብቻ ሂሳብ መዝገብ መዘጋጀት የሚጠበቅ ሲሆን፤ የካታል ሀብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅምም ቢሆን በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ -59 የካፒታል ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም እንደተደነገገዉ የምድብ " ሀ" ግብር የሚከፈልባቸዉ ሀብቶች 15% (የማይንቀሳቀሱ ሀብቶች) እና ምድብ " ለ" ግብር የሚከፈልባቸዉ ሀብቶቸ 30% (ቦንድና አክሲዮኖች) ሲሆን፤ በተናጠል ሂሳብ መዝገብ መያዝ ይኖርበታል።
- በተለይም የቤት ኪራይ ገቢ ከመደበኛ ገቢ ጋር ተደምሮ እየቀረበም ስላለ ስለሆነ መስተካከል አለበት።

3.2 የቤት ኪራይ ገቢ

ግብር የሚከፈልበት ኪራይ ገቢ፤

- የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ የኪራይ ገቢ ነው የሚባለው ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ ቤት በማከራየት ካገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀደው ጠቅላላ ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀረው ገቢ ነው።

የተከራይ አከራዮች

- የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው፤ የሚባለው የተከራይ አከራዩ በግብር ዓመቱ ከተቀበለው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ ላይ ለዋናው አከራይ የሚከፍለው ኪራይ እንዲሁም ገቢውን ለማግኘት ያወጣቸው ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ነው።
- ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ሳይከፍል ቢቀር ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል።

3.3 የሚከራይ አዲስ ቤትን ስለማሳወቅ

- ለኪራይ የሚሰራ ቤት ተሰርቶ እንዳለቀ ወይም ቤቱ እንደተከራየ፣ ከሁለቱ በሚቀድመው ጊዜ የቤቱ ባለቤትና የቤቱ ሥራ ተቋራጭ የቤቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ወይም የተከራየ መሆኑን ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ያለበትን ሰው ስም፣ አድራሻና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ቤቱ ለሚገኝበት የቀበሌ አስተዳደር ወይም የአካባቢ አስተዳደር ማስታወቅ አለባቸው።
- የቀበሌው አስተዳደር እና የአካባቢው አስተዳደር በማስታወቂያው መሰረት የተገኘውን መረጃ ለግብር ሰብሳቢው አካል መግለጽ አለባቸው።
- ከአከራዩ ጋር ከገባው ውል ውጪ በገዛ ፍቃድ የተከራየውን የንግድ ስራ ሀብት በራሱ ወጪ የሚያድስ፣ የሚጠግን ወይም የሚያሻሽል ተከራይ ለዕድሳቱ ለጥገናው ወይም ለማሻሻያ ያደረገው ወጪ ከንግድ ሥራ ገቢው ላይ ተቀናሽ ይደረግለታል።

3.4 የካፒታል ሀብቶችን ስለማስተላለፍ

የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር *979/2008* አንቀጽ *59* እና የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር *8/2011* መሰረት የተዘጋጀ፡-

- አንድ ሰው በግብር ዓመቱ ውስጥ አንድን ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲያስተላልፍ ኪሳራ የደረሰበት እንደሆነ ኪሣራው በዚያው የግብር ዓመት በተመሳሳይ ምድብ ያለ ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲያስተላልፍ ከሚገኘው ገቢ ጋር እንዲቻቻል ይደረጋል፡-

  ሀ) ኪሳራው የሚውለው የተገኘን ገቢ ለማስቻል ነው፣

  ለ) ያልተቻቻለው ኪሳራ ተቻችሎ እስከሚያልቅ ድረስ

  በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ ያለ ሀብት በሚተላለፍበት ጊዜ

  ለማካካስ እንዲውል ላልተወሰነ ጊዜ ይሸጋገራል፣

  ሐ) አንድ ሰው ግንኙነት ላለው ሰው ሀብት ያስተላለፈ እንደሆነ

  ኪሳራ ዕውቅና አይሰጠውም፣

  መ) አንድ ሰው የደረሰበትን ኪሳራ ገቢ ሰብሳቢው በሚያሳምን

  መንገድ ማስረዳት የቻለ እንደሆነ።

3.4 የካፒታል ሀብት.....

የካፒታል ሀብትን በማስተላለፍ ከተገኘው ጠቅላላ ጥቅም ውስጥ በንግድ ስራ ገቢ ወይም/ እና በቤት ኪራይ ገቢ ውስጥ የሚካተተው እና በአዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 59 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ መጠን ቀጥሎ በተመለከተው ቀመር የሚሰላ ይሆናል።

ረ = ሀ-(ለ*መ)

ሠ = ለ - ሐ

<u>ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፡-</u>

ሀ) ሀብቱ የተሸጠበት ዋጋ

ለ) ሀብቱ የተገኘበት/የተገዛበት ዋጋ (ለሀብቱ የተደረገ ወጪን ጨምሮ)

ሐ) የሐብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ

መ) የግሽበት ማስተካከያ

ሠ) ከሀብቱ ሽያጭ ከተገኘ ጠቅላላ ጥቅም ወይም ከደረሰ ኪሳራ ውስጥ በንግድ ስራ ገቢ ወይም / እና የቤት ኪራይ ገቢ ውስጥ የሚካተት ገቢ ወይም ተቀናሽ የሚደረግ ኪሣራ፣

ረ) ከሀብቱ ሽያጭ ከተገኘ ጥቅም የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ ግብር የሚከፈልበት ገቢ፣

3.4 የካፒታል...

ምሳሌ1፡- የህንጻ ካፒታል ጌይን ማሳያ

Sale of Capital Asset (Building with Gain)

ሀ. የንግድ የህንጻው የሽያጭ ዋጋ 120,000,000.00

ለ. የንግድ ህንጻዉ የተገዛበት ዋጋ 85,000,000.00

- ህንጻዉ የተገዛበት ጊዜ ሐምሌ 5/2005 ዓ.ም
- ህንጻዉ የተሸጠበት ሰኔ 30//2013 ዓ.ም (ግንኙነት ለሌለዉ ግብር ከፋይ የተሸጠ)

ሐ. የህንጻዉ የመዝገብ ዋጋ 51,000,000.00

መ. የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ 15,000,000.00 (Let Assume—Data from Bank)

3.4 ካፒታል ጌይን...

የንግድ ህንጻ በሽያጭ ሲተላለፍ፤-

የተጣራ መዝገብ ዋጋው= Original Cost-Accumulated Depreciation

85,000,000 – 34,000,000 = 51,000,000

የተገኘ ጠቅላላ ጥቅም

=የተሸጠበት ዋጋ - (የተጣራ መዝገብ ዋጋው + የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ)

= 120,000.000 - (51,000,000+15,000,000)= 54,000,000፤ Total gain

የካፒታል ዋጋ ጥቅም ግብር

=(የተሸጠበት ዋጋ (Sale) – (የመጀመሪያ ዋጋ ብር (OC) + የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ))*15%

= (120,000,000 - (85,000,000+15,000,000)) *15% = 3,000,000

ለንግድ ሥራ ገቢ ግብር

=(ህንፃ የተገዛበት ዋጋ – የተጣራ መዝገብ ዋጋው)*35 %-18000

= (85,000,000-51,000,000)*35 %-18000 = 5,082,000.00

3.4 የካፒታል...

- የካፒታል ሀብት በስጦታ፤ በእርዳታ፤ በዓይነት መዋጮ ወይም በድርሻ መልክ ሲተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ የተቀባዩ ስለሆነ ይህ ስለመከናወኑ በመዝገብ መያዝ አለበት።

3.5 የግብር ሰንጠረዦች

ሰንጠረዣዉ /Schedular/ የግብር/ታክስ ስርዓት፡-

አገራችን ሰንጠረዣዉ /Schedular/ የግብር ስርዓት ተከታይ ስትሆን፤ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 8 ድንጋጌ መሰረት፡-

ሀ) ሰኝጠረዥ "ሀ " ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ።

ለ) ሰኝጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ።

ሐ) ሰኝጠረዥ "ሐ" ከንግድ ስራ የሚገኝ ገቢ።

ሐ) ሰኝጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች።

መ) ሰኝጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር ነጻ የሆኑ ገቢዎች።

3.5 የሰንጠረዥ "መ“ ገቢዎች፤

ስለሆነም የሰንጠረዥ "መ" ን በዝርዝር ለማየት ያህል፡-

- ሰኝጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች ፤ነዋሪ ከሆኑና ካልሆኑ እንዲሁም የታክስ ምጣኔዉን በተመለከተ አተገባበሩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 51 እስከ 64 በግልጽ ተደንግጎ የሚገኝ ነዉ። በዚህ ሰነድ ይህንን ዝርዝር ለማብራራት ሳይሆን ከሂሳብ መዝገብ አያያዝ ጋር በተያያዘ ጉዳዩ የሚገናኝ በመሆኑና መሰረታዊም ስለሆነ ፤ ግብር ከፋዮች እነዚህ ገቢዎች በስራቸዉ አጋጣሚ ሲከሰቱ ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በምን መልኩ እንደሚያሳዉቁ ለመግለጽ የተዘጋጀ ነዉ።
- በመሆኑም ከሰንጠረዥ "ሀ" እስከ ሰኝጠረዥ "ሐ" የሚገኙ ገቢዎች ላይ የሚከፈል ግብርን ለግብር ሰብሳቢዉ መ/ቤት ግብር ከፋዩ፤ በማስታወቅ /By declaration/ መሰረት የሚከፍለዉ ግብር ሲሆን፤ ሰኝጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎችን እንደየገቢ ባህሪያቸዉ በማስታወቅ /By declaration/ እና ቀንሶ በማስቀረት /Withholding Scheme/ ግብር ይከፈላል ማለት ነዉ።

3.5 ሰንጠረዥ.....

- ስለሆነም ሰኝጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር ነጻ የሆኑ ገቢ በመሆናቸዉን ማስታወቅን ወይም ቀንሶ ማስቀረትን የማይጠይቁ ናቸዉ። በመሆኑም ነዋሪ የሆኑና ያልሆኑ ሰዎች ባገኙት ገቢ ላይ ግብር እንደሚከፍሉ በሰኝጠረዥ "መ" የተመላከተ ሲሆን፤ ግብር ከፋዮች በምን መልኩ ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት እንደሚያሳወቁት ለመግለፅ ሲሆን የማስታወቅ ዘዴዎቹም፤ ግብር ከፋዩ ለግብር አሰገቢዉ መ/ቤት በማስታወቅ /Per Declaration/ እና ቀንሶ በማስቀረት /Withholding/ ስለሆነ ነዉ። በማስታወቅ ሲባል በቀጥታ አገልግሎት /መብቱን/ የተጠቀመዉ ነዋሪ የሆነና ያልሆነ ሰዉ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በሚያቀርብለት የታክስ ማሳወቂያ ቅጽ መሰረት የሚያሳዉቀዉ ሲሆን፤ በቀንሶ ማስቀረት ማለት ደግሞ አገልግሎት/መብቱን/ የተጠቀመዉ ነዋሪ የሆነና ያልሆነ ሰዉ በቀጥታ ለማስታወቅ የማይቻልበት በመሆኑ መነሻነት አገልግሎት/መብት/ ባገኙት ግብር ከፋዮች በኩል በክፍያ ወቅት ቀንሰዉ ግብሩን ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት የሚያሳወቁበት መንገድ ነዉ።
- ስለሆነም ግብር ከፋዮች ከመደበኛ ገቢያቸዉ ባለፈ በንግድ እንቅስቃሴ ወቅት የሰኝጠረዥ "መ" ገቢዎችን እንደሚከተለዉ ያሳዉቃሉ። ስለሆነም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 64 ድንጋጌ መሰረት በሰንጠረዥ "መ" መሰረት የሚጣል ግብር በሌሎች ሰንጠረዦች ስር ግብር ለሚከፈልበት ገቢ ወይም ከገቢ ግብር ነጻ በኖኑ ገቢዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም። ስለሆነም በዚህ ሰንጠረዥ ላይ የሚጣለዉ ግብር በገቢዉ ላይ የመጨረሻ ግብር ይሆናል።

የሰንጠረዥ "መ" ገቢዎችን ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ የሚስታወቅ ዘይ፤

ተ.ቁ	የሰንጠረዥ "መ" የታክስ ዓይነቶች	ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ የግብር ማስታወቅ ዘይዉ (በማስታወቅ ወይስ ቀንሶ በማስቀረት)	ማብራሪያ
1	ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች/Non Residents/	ቀንሶ በማስቀረት (Withholding Scheme)	With some Exception of "Declaration"
2	እንዲተካ በተጠየቀ የቴክሊክ አገልግትና ሮያሊቲ ክፍያ	ቀንሶ በማስቀረት (Withholding Scheme)	
3	ነዋሪ ያልሆኑ የመዝናኛ አገልግሎት ሰጭዎች ግብር	ቀንሶ በማስቀረት (Withholding Scheme)	
4	ሮያሊቲ (Royality)	በቀጥታ በማስታወቅ (Declaration Scheme)	
5	የትርፍ ድርሻ (Devidend)	ቀንሶ በማስቀረት (Withholding Scheme)	
6	ወለድ (Interest)	ቀንሶ በማስቀረት (Withholding Scheme)	
7	የእድል ሙከራ (Games or Chance)	ቀንሶ በማስቀረት (Withholding Scheme)	
8	ሀብትን አልፎ አልፎ ማከራየት (Causal income)	በቀጥታ በማስታወቅ (Declaration Scheme)	
9	የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ /Gain On Disposal/	በቀጥታ በማስታወቅ (Declaration Scheme)	With Schedule "C" and Independent Statement
10	ንፋስ አመጣሽ /Wind fall Profit/	ቀንሶ በማስቀረት (Withholding Scheme)	
11	ባልተከፋፈለ ትርፍ/Undisributed Profit/	ቀንሶ በማስቀረት (Withholding Scheme)	
12	በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት የሚላክ ትርፍ	በቀጥታ በማስታወቅ (Declaration Scheme)	
13	ሌሎች ገቢዎች።	እንደሁኔታዉ (As per The Case)	

3.6 የሂሳብ መግለጫ

ከሂሳብ መግለጫ በተጨማሪነት ግብር ከፋዩ ሊይዛቸዉ የሚገቡ ሰነዶች፡-

- የንግድ ስራ ሀብት መዝገብ
- የእዳ እና ተከፋይ ሂሳቦች መዝገብ/*Book of Liability/*
- የካፒታል ሂሳብ መዝገብ
- ጊዜያዊ የታክስ የሂሳብ መዝገብ/*Temporary Book of Account/*

ግብር ከፋዩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የታክስ የሂሳብ መግለጫበማዘጋጀት ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

- *Balance Sheet or Statement of financial Position*
- *Cash Flow Statement.*
- *Capital Statement.*
- *Profit or loss and Other Comprehensive Income.*
- *Production Statement.* (የምርት ሂደት መግለጫ)
- *Statement of cost of goods Manufactured.* (የምርት ዉጤት መግለጫ)

3.7በሂሳብ መግለጫ ስለሚደረግ ማስተካከያ

5.1 <u>ሂሳብ መግለጫ ላይ በሚደረግ ማስተካከያ፤</u>

- ወደ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ በግብር ከፋዩ የሚያቀርቡት ሂሳብ መግለጫዎች ፤ በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ በኩል <u>ተቀባይነት የሚያገኝ፤</u> <u>ማስተካከያ የሚደረግበት</u> ወይም <u>ተቀባይነት ሊያጣ</u> የሚችልበት አግባብ ሊኖር ይችላል።

<u>ምሳሌ፡-</u>

- XYZ የተባለ ግለሰብ በአስመጭነት ንግድ ስራ የተሰማራ ግብር ከፋይ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫ ለተመዘገቡበት ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት መስከረም 20 ቀን 2012 ዓ.ም አሳዉቀዋል፡- ያሳወቁት የትርፍና ኪሳራ መግለጫ በዋናነት ሲታይ፡-

ግብር ከፋዩ ለ2011 በጀት ዓመት ያሳወቁት የትርፍና ኪሳራ መግለጫ

Sales			**21,000,000.00**
	Beginning Inv.	5,700,000.00	
	Purchases	18,000,000.00	
	Available For Sale	23,700,000.00	
	Ending Inventory	7,000,000.00	
Cost of Goods Sold			16,700,000.00
Gross Profit			4,300,000.00
Gen.& Adm Expense			850,000.00
Net Profit			3,450,000.00
Profit Tax			1,189,500.00
Net Profit After			

3.8 የሂሳብ ማስተካከያ

ሆኖም የግብር ከፋዩ የሂሳብ መግለጫ በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ በሚታይበት ወቅት፤የሚከተሉት ማስተካከያዎች ነበሩበት፡-

ሀ) ከዚህ ቀደም በእጅ በእጅ የተ.እ.ታ ደረሰኝ ቁጥር Fs No. 0000125 ቀን መጋቢት 5/2011 ዓ.ም ለተፈጸመ ሽያጭ ብር 350,000.00 (ከተ.እ.ታ በፊት) ሂሳብ መግለጫዉ ላይ አልተካተተም፤

ለ) በ2011 በጀት ዓመት በቆጠራ የተረጋገጠ የእቃ ዋጋ ብር 7 ሚሊዮን ብር ሳይሆን 6 ሚሊዮን 8 መቶ ሃምሳ ሽ ብር ብቻ መሆኑ በመረጋገጡ፤

ሐ) ግብር ከፋዩ በአስተዳደራዊ ወጭነት ለበጀት ዓመቱ ያሳወቁት ብር 850,000.00 ሲሆን ህጋዉ ደረሰኝ የቀረበለት ግን ብር 750,000.00 ብቻ መሆኑ ፤

የሚሉት ግኝቶች ብቻ በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ የተረጋገጠ ቢሆንና ከዚህ ወጭ ሌላ ተጨማሪ ክፍተት የሌለዉ ሂሳብ መግለጫ ነዉ ያሳወቁት ብለን ብናስብ፡- ግብር ከፋዩ ያሳወቁት ሂሳብ መግለጫ ዉድቅ ሳይደረግ እነዚህ ማስተካከያዎች በሚከተለዉ መሰረት ይደረጋሉ ማለት ነዉ።

ማዕተካከያ የተደረገበት ለ2011 በጀት ዓመት የቀረበ የትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ

Sales			**21,350,000.00**
	Begining Inv.	5,700,000.00	
	Purchases	18,000,000.00	
	Avilable For Slae	23,700,000.00	
	Ending Inventory	6,850,000.00	
Cost of Goods Sold			16,850,000.00
Gross Profit			4,500,000.00
Gen.& Adm Expense			750,000.00
Net Profit			3,750,000.00
Profit Tax			1,294,500.00
Net Profit After tax			2,455,500.00

3.9 በሂሳብ መዝገብ መሰረት በማድረግ የሚወሰን የታክስ ስሌት ላይ የሚከሰት ስህተትን ስለማረም፡-

- የታክስ ባለስልጣኑ ግብር ከፋዩ የሚያቀርበዉን የሂሳብ መዝገብ መሰረት በማድረግ የታክስ ስሌት ሲወስን የሚከሰቱ ስህተቶችን ማረም የሚችለዉ **በታክስ ህግ ወይም በጉዳዩ ኩነቶች የትርጉም ጥያቄ የማያስነሳ የአጻጻፍና የሂሳብ ስሌት እንዲሁም የማያከራክሩ ስህተቶች ሆነዉ ሲገኝ ነዉ**። በመመሪያ ቁጥር 152/2011 አንቀፅ-37 ንኡስ አንቀጽ-1 የተደነገገ እና መነሻዉም የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንፅ 85 ስህተቶችን ስለማረም ድንጋጌ ነዉ)።
- በመሆኑም የሚታረሙት ስህተቶችን ዓይነት በተመለከተ፡-
- የመደመር፤ የመቀነስ፤ የማባዛትና የማካፈል ስህተት፤
- የስሌት ማጠቃለያና መንደርደሪያ መካከል የሚከሰት ስህተት፤
- የቁጥሮች የቦታ መቀያየር/Transposition/
- የቃላት አገባብ ስህተት /Grammer Error/
- በደረሰኝ ወይም በሌላ ማስረጃ የተመላከተ ሂሳብን ሳይደምሩ ወይም ሳይቀንሱ መዝለል፤ መተዉ /Ommission/ ወዘተ...ለማሳያነት ሲቀሱ ለዝርዝር በመመሪያዉ አንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ 2 ተመላክቶ ይገኛል/።በመሆኑም ስህተቱን ለማረም የአሰራር ሂደቶች ያሉት ሲሆን፡-

አመሰግናለሁ !!!

